## የልጅ ማፈላለግ ዓላማ መግለጫ

የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የልጅ ማፈላለግ አላማ የእድገት ችግር ወይም ጉዳት አለባቸው ተብለው የሚጠረጠሩ ልጆች በማፈላለግ ግምገማ ማድረግ ነው። ልጁ ያለው የአካል ጉዳት በመማር ሂደት ላይ ችግር ይፈጥራል ተብሎ ከተወሰነ የቅድመ-መደበኛ ልዩ ትምህርት(ECSE) እና/ወይም ተጨማሪ አገልግሎቶች እንዲያገኝ ሃሳብ ሊቀርብ ይችላል። ሌሎች አገልግሎቶች የሚከተሉትን ያካትታል ነገር ግን በእነዚህ ብቻ አይወሰነም፤ የንግግር/ቋንቋ ቴራፒ ፣ የአካል ቴራፒ ወይም አኮፔሽናል ቴራፒ ።



### ማን ነው ልጆችን ለአገልግሎት የሚልከው?

አንድ ልጅ ወደ ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ልጅ ማፈላለግ፤ በማናቸውም በሚከተሉት ሰዎች ሊላክ ይችላል፤

- በወላጅ/ሕጋዊ አሳዳጊ፣
- በቤተሰብ አባል ወይም ጎደኛ
- በሐኪም
- በት/ቤት ሠራተኞች
- በህፃናት መዋያ አገልግሎት ሰጪ
- የኮሚዮኒቲ ድርጅቶች
- በኢንፋንት ቶድለር ኮኔክሽን -ፓረንት ኢንፋንት ኢዱኬሽን(ITC-PIE) ሰራተኞች

**የወላጅ/ ህጋዊ አሳዳጊ ተሳትፎ ያስፈልጋል በቀጣይ በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ስራ ለመስራት።**

### ተጨማሪ ሪሶዋርሶች፤

- **ቨርጂኒያ ትምህርት ዲፖርትሜንት ቅድመልጅነት ( Virginia Department of Education Early Childhood)**
  http://www.doe.virginia.gov/early-childhood/preschool

- <u>**የልዮ ትምህርት የወላጆች መመሪያ (Parent's Guide to Special Education)**</u>
  Virginia Department of Education
  http://www.doe.virginia.gov/special_ed/parents/parents_guide.pdf

- **በኢንፋንት ቶድለር ኮኔክሽን -ፓረንት ኢንፋንት ኢዱኬሽን (Infant & Toddler Connection – Parent Infant Education Program (ITC-PIE) (እድሚያቸው ከ0 እስከ 3)**
  https://www.infantva.org or **703-746-3350**

- **የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ት/ቤቶች ማውጫ (ACPS School Directory ) (እድሚያቸው ለትምህርት ለደረሰ ከ5 እስከ 22 ዓመታት)**
  https://www.acps.k12.va.us/ourschools or 703-619-8000

**የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ልጅ ማፈላለግ (Child Find)፤**
**ለተጨማሪ መረጃ እባክዎን**
**(703) -578-8217 ፣ ወይም**
**Childfind@acps.k12.va.us ይገናኙ።**

**ልጅ ማፈላለግ፤**
**እና፤**
**ቅድመ-ሕጻናት ልዩ ትምህርት አገልግሎቶች**

ጀፈርሰን ሂውስተን ት/ቤት
1501 Cameron Street, Room 235
Alexandria, VA 22314

ACPS
Alexandria City Public Schools

# ልጅ ማፈላለግ እና የቅድመ-ሕጻናት የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች

CHILD FIND

**ስለ ልጅ እድገት ለእርስዎ ጥያቄዎች መልስ በመስጠት እኛ ልናግዝ እንችላለን ።**

የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የልጅ ማፈላለግ በሴፕቴምበር ወር ሁለት ዓመት እና በትምህርት ዓመቱ እስከ አምስት ዓመት የሚሟላቸው (ከመዋእለ ህፃናት በፊት) የእድገት ችግር ወይም ጉዳት እንዳላቸው የሚጠረጠሩ የእርሱ/ሷ የትምህርት አቀባበል ወይም የትምህርት አቀባበል ላይ ተእፅኖ ሊያሳድር እንደሚችል የሚገመቱ ልጆችን በነፃ የልጆች የመለየት እና/ወይም የመገምገም ስራ ያከናወናል።

## ስም ማስተላለፍ

**የልጅ ማፈላለግ ቡድን  እድሚያቸው ከ2 እስከ 5 የደረሱ የእድገት መዘግየት ወይም ጉዳት ችግር አለባቸው ተብሎ የሚገመቱ ልጆችን በነፃ የመመለየት እና ግምገማዎች አገልግሎት ይሰጣል።**



### አንድ ልጅ መቼ ነው ወደ ልጅ ማፈላለግ ስሙ የሚተላለፈው?

- አንድ ልጅ የእድገት ሚዛኖችን፣ በንግግር፣ አካል እድገት፣ አስተሳሰብ/ምክንያት፣ ራስን በማገዝ እና/ወይም በማህበራዊ አግባብ ችሎታዋች ማሟላት ካልቻለ/ካልቻለች

- አንድ የአካል ችግር ወይም የህክምና ችግር በልጁ የእድገት እና/የመማር ችሎታዋች ላይ ተፅእኖ የሚያሳድር ከሆነ።

**ማስታወሻ፤** ተማሪዋች የተወሰኑትን ባህሪዋች ሊያንፀባርቁ ነገር ግን ሁሉንም የተጠቀሱትን  ባህሪዋች ላያሳዩ ይችላሉ።  በልጁ የመማር ችሎታ ተፅእኖ የሚያሳድር ማንኛውም ሁኔታ ስሙን ለማስተላለፍ ምክንያት ሊሆን ይችላል።  አሳሳቢ ሁኔታዋች እላይ በተገለፁት ዝርዝር ብቻ የሚወሰን አይደለም።

## የማጣራት ስራ

**የወላጅ/አሳዳጊ የልጁ እድገት በሚመለከት ከልጅ ማፈላለግ ስራተኛ ጋር ይወያያል ።**

**የእድገት መገለጫዋች በሚመለከት ልጁን የመመርመር ስራ ይካሄዳል  በቅድመ-ህፃናት ልዮ ትምህርት አስተማሪዋች**

- የመግባባት ችሎታዋች በተመለከተ
- የማመዛዘን/የማስብ ችሎታዋች
- ራስን የማገዝ/አዳፐቲቭ ችሎታዋች
- የግል ማህበራዊ ችሎታዋች
- የአካላዊ እንቅስቃሴ ችሎታዋች

ሰራተኞች ከወላጆች/አሳዳጊ ጋር በመሆን የተገኘውን ውጤት ይመረምራሉ የእርሱ/ሷን  ትምህርት ለማገዝ በቀጣይነት  ስለሚደርጉ ነገሮች ይወያያሉ ።

**የሚከተሉት ሰነዶች ያስፈልጋሉ፤**

- የአሌክሳንደሪያ ኖሪነት ማረጋገጫ(ሁለት ሰነዶች)
- የልጁን ዋና የትውልድ የምስክር ወረቀት፣
- የወላጅ/አሳዳጊ፤ መታወቂያ ወረቀት(መንጃ ፈቃድ ወይም ፓስፖርት) ወይም ህጋዊ የአሳዳጊነት ሰነድ (አስፈላጊ ከሆነ)

### እንዴት ነው  የሚጀመረው?፤

**እባክዎን  ከኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ልጆች ማፈላለግ ( Child Find) በስልክ 703-578-8217  ወይም childfind@acps.k12.va.us ይገናኙ።**

አ

## አሰራር ሂደት

**በልጅዎ የማጣራት ስራ ላይ ተመስርቶ ተጨማሪ ምርመራ እና ጣልቃ የመግባት ስራ አስፈላጊ ከሆነ ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ቀጣይ የሆነ ስብሰባ እንዲኖር ሃሳብ ሊያቀርብ ይችላል ተጨማሪ ምርመራ እና ጣልቃ የመግባት ስራ አስፈላጊ ከሆነ።**

### የመጀመሪያ ደረጃ ፤ የልጅ ጥናት ስብሰባ፤

- ወላጅ/ አሳዳጊ ባሉበት ቡድኑ የልጁን ጥንካሬና ፍላጎት ይመለከታል።
- ተጨማሪ ምርመራ ወይም ክትትል አስፈላጊ ስለመሆን ውሳኔ ላይ ይደርሳል።
- ተጨማሪ ምርመራ ለማድረግ የወላጅ/ አሳዳጊ ስምምነት ያስፈልጋል።

### ሁለተኛ ደረጃ፤ የምርመራ ቀጠሮ(ዋች)

- ጉዳት አለ ተብሎ የሚጠረጠሩ ጉዳዮች በተመለከተ ምርመራ ይደረጋል።

### ሦስተኛ ደረጃ፤ የብቁነት ስብሰባ (ስማቸው በተላለፈ ባሉት 60 ቀናት ውስጥ)

- ቡድኑ የምርመራውን ውጤት ከወላጅ/አሳዳጊ  ጋር አብረው ይመለከታሉ።
- የተጠረጠረ ጉድለት በሚመለከት የብቁነት መስፈርት ማጥናት፤

### አራተኛ ደረጃ ፤  ብቁ ከሆነ የግል የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ስብሰባ  (ብቁ ከሆኑ በኋላ በ30 ቀናት ውስጥ)

- ወላጅ/ አሳዳጊ ባሉበት ቡድኑ የልጁን ጥንካሬና ፍላጎት ይመለከታል።
- በግል የትምህርት ፕሮግራም (IEP) የተዘጋጁ ዓመታዊ ግቦችን ይመለከታል።
- የክለሳ አገልግሎቶች
- አገልግሎቱን ተግባራዊ ለማድረግ የወላጅ/ አሳዳጊ ስምምነት ያስፈልጋል።